# የትምህርተ ሥላሴ መሠረታውያን

ከተስፋዬ ሮበሌ

ወርኀ መስከረም፤ 2025 ዓ.ም

አትላንታ ጆርጂያ

## በዕንቊጣጣሽ ማግስት 2018 ዓ.ም

እንደ ኢትዮጵያውያን የዘመን ቀመር

# አስተምህሮውን በተመለከተ በሥላሴ አማንያን መኻል ያለው አለዋቂነት እጅግ ሲበዛ ጥልቅ ነው

- እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን ቀመር በ2002 ዓ.ም፣ በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መኻል የተካሄደ አንድ ጥናት፣ ከሳውስቱና መነኮሳቱ በአስተምህሮው ላይ የተዛባ አመለካከት እንዳላቸው ከማሳየቱ ባሻገር፣ የጥናቱ ውጤት ለብዙዎች አስገራሚ አስደንጋጭም ሆኖ ዐልፎአል።

- ጥናቱ ደረስሁባቸው ከሚላቸው ስታቲስቲካዊ ግኝቶች መኻል አንዱ እንደሚከተለው ይነበባል:—

  - ከእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መኻል ትምህርተ ሥላሴን በተመለከተ አጥጋቢ ማብራሪያ ማቅረብ የሚችሉት፣ ሰባ ስምንት ከመቶ (78%) የሚሆኑ ወንድ ቀሳውስት፣ ሰባ ከመቶ (70%) የሚሆኑ ሴት መነኮሳት ብቻ ናቸው።






- ይህ በቀሳውስቱና በመነኮሳቱ ማለት በቤተ ክርስቲያን የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች መኻል ያለው ግራ መጋባት ነው። ትምህርቱን ባለማወቅ እንዲሁም በተቃራኒ ወገን የሚቀርቡ ትችቶችን መቋቋም ባለመቻል ሥላሴአዊ እምነቱን እየጣለ መናፍቃዊ ድርጅቶችን የሚቀላቀለው የሕዝብ ቊጥር እጅግ ሲበዛ አስደንጋጭ ነው።

- ድርጅቱ አራት ሚሊዮን አባል አለኝ እንዲሁም እንቅስቃሴውን ከጀመርሁ 54 ዓመት ሆኖኛል ከሚለው ጋር ዐዋጁ ጋር፣ ቊጥሩን ስናነጻጽር በ54 ዓመት ውስጥ፣ 75 ከመቶ የሚሆኑ ማለትም ሦስት ሚሊሆን የሚሆኑ ሰዎች የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ጥለው በመሄድ፣ ከሰባልዮስን ኑፋቄ ጋር ተቀላቅለዋል።




Breakdown of 60,000 per Year
Value
60000
50000
40000
30000
20000
10000
0
60,000.00
5,000.00
164.38
6.85
Yearly
Monthly
Daily
Hourly



Growth of 'Jesus Only' Movement in Ethiopia (54 years)
Estimated Growth of 'Jesus Only' Movement
Members (millions)
0.0M
0.5M
1.0M
1.5M
2.0M
2.5M
3.0M
3.5M
4.0M
0
5
10
15
20
25
30
35
40
45
50
Years since founding

# ልብ ይሏል:—

- ይህ “ከኦንሊ ጂሰስ” አንጻር ብቻ ያለ ዘገባ ነው፤ ነገር ግን ወደ “ይሖዋ ምስክሮች” እንዲሁም ወደ እስልምና የሚሄደውን ቊጥር ካሰላን እጅግ ሲበዛ ጭንቅላት ይበጠብጣል፤ ጭንቅላት ላለው ሰው።

- በአሜሪካና በዐዲስ አበባ በሚገኙ ሰባት ቤተ ክርስቲያናት ዘንድ የተካሄደ አንድ ጥናት፣ ትምህርተ ሥላሴን፣ ትንሣኤ ሙታንን፣ ነገረ ክርስቶስን፣ ነገረ ድነትን በትክክል ማብራራት የሚችሉ ሰዎች ከመቶ 7 እጅ የሚሆኑቱ ብቻ ናቸው።



ምን እንደሚያምኑ የሚያውቁ እንዲሁም ለምን በዚያ መልክ ማመን እንዳለባቸው ምክንያታዊ ማስረጃም ሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት ድጋፍ ማቅረብ የሚችሉ 7 ከመቶ የሆኑቱ ብቻ ናቸው (በተለያዩ ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ላይ)።



- 27 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ምን እንደሚያምኑ ያውቃሉ (ትምህርተ ሥላሴን፣ ትንሣኤ ሙታንን፣ ነገረ ክርስቶስን፣ ነገረ ድነትን)፤ ነገር ግን ለምን በዚያ መልክ እንደሚያምኑ ምክንያታዊ ማስረጃም ሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ ማያቀርብ አይችሉም።



# የትምህርተ ሥላሴ ታሳብያን መሠረቶች

ከዚህ በታች የሚገኙት ሰባት ነጥቦች፣ ይህ ዐውደ ጥናት አንዳችም ማስረጃ የማያቀርብባቸው ነገር ግን እውነተኝነታቸውን መነሻ አድርገን ትምህርቱን የምናዋቅርባቸው፣ መሠረታውያን ነጥቦች ናቸው። እነሆ:—

፩. ለፍጥረቱ ሁሉ መገኛ የሆነ ዘላለማዊ አምላክ አለ።

፪. እውነት ነባራዊ እንጂ፣ አንጻራዊ አይደለችም። እውነት በሰዎች ስምምነት፣ ፍላጎት ወይም ባህል የሚወሰን አንጻራዊ ጉዳይ ሳይሆን በጊዜ፣ በቦታና በሁኔታ የማይለወጥ ነባራዊ ሐቅ ነው።

፫. አምላክ ራሱን እንዲሁም ፈቃዱን ለፍጥረቱ ገልጾአል።

፬. እግዚአብሔር አምላክ ራሱን በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ገልጾአል።

፩. ብሉያትና ሐዲሳት ሕጸጽ አልባ የአምላክ አፊዎተ ቃል እስትንፋሰ እግዚአብሔር ናቸው።

፪. ቅዱሳት መጻሕፍትን በትክክል ለመረዳት ብሎም ለመተንተን ታሪካዊ፣ ሰዋስዋዊና ሥነ ጽሑፋዊ የትርጓሜ ሥልት ትክክለኛ የፍታቴ ሕግ ነው።

፫. አምላክ የቅራኔ አምላክ አይደለም። ስለዚህ እርስ በርስ የሚቃረኑ ዐዋጆች አንዱ አለያም ሁለቱም ስሕተት ናቸው።




# የዐውደ ጥናቱ ቀዳማይ ግብ



በርግጥ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት ላደረጉ ክርስቲያኖች፣ ትምህርተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ማሳወቅ።



አስተምህሮውን ለሚጻረሩ ምልከታዎች ከትካች ዐጸፋ መሰንዘር።



ታዳሚው ይህን መሠረተ እምነት እንዲቀበል የተቀበለውም እንዲያውጀው ማበረታታት።

# በሕግ አምላክ ቃል አጠቃቀሙ

- ሥላሴ የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሌለ፣ አስተምህሮውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

**ይስተካከል!**

- ✓ እውነት ነው "ሥላሴ" የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም፤ ይህ ግን ትምህርተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፣ ወደሚለው ድምዳሜ አያደርስም።
- ✓ በመሠረቱ "የይሖዋ ምስክሮች"፣ "የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን"፣ ወዘተ የሚሉትም ስያሜዎች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉም። እነዚህ ስያሜዎች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሌሉ ብቻ፣ እነዚህ ቤተ እምነቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም ማለት ስሕተት ነው።
- ✓ በመሠረቱ "ትምህርተ እግዚአብሔር"፣ "ነገረ ክርስቶስ"፣ "ሥነ ፍጻሜ" ወዘተ የሚሉም ስያሜዎች ቃል በቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰው አናገኝም። እነዚህ ስያሜዎች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሌሉ ብቻ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት በእነዚህ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ትምህርት የላቸውም ማለት ስሕተት ነው።

# የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትና የነገረ መለኮት መዝገበ ቃላት

- “አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ” የሚለው ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሲሆን፣
- “ሥላሴ” የሚለው ደግሞ፣ የነገረ መለኮት ስያሜ ነው።
- የመጀመሪያውን በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ የምናገኘው ሲሆን፣
- ሁለተኛውን ደግሞ የነገረ መለኮት መዛግብተ ቃላት ላይ፣ ሐተታ ቀርቦለት እናገኘዋለን።
- መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀጥታ ተጠቅሰው የምናገኛቸው ቃላት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ሲሆኑ (ለምሳሌ ሙሴ፣ እስራኤል፣ ምኩራብ፣ ሰዱቃውያን፣ ገላትያ ወዘተ)፣
- ነባብያነ መለኮት ደርዛዌ ነገረ መለኮትን ለማብራራት የሚጠቀሙባቸው ሙያዊ ስያሜዎች ደግሞ የነገረ መለኮት ቃላት ይባላሉ።

# የቋንቋ ፍልስፍና

- ቃላት ነባራዊ ትርጒም የላቸውም። ተናጋሪው ማኅበረሰብ የሚሰጣቸውን ትርጒም ወክለው ግልጋሎት ላይ ይውላሉ። በዚህም አግባብ ነው፣ "ቃላት የስምምነት ውጤት ናቸው" የሚባለው። ስለዚህ አንድ ሰው አንድ ቃል በተለየ አግባብ ቢጠቀም፣ ምን ማለት ፈልገህ ነው ተብሎ ሊጠየቅ ይገባል። ነገር ግን እኛ በምፈልገው መልክ አልተጠቀማችሁምና የቃላት አጠቃቀማችሁ የፅንሰ ዐሳብ እክል አለው ማለት ስሕተት ነው።

- የአሜሪካው ቢሮ የበላይ ጠባቂ David K. Bernard ሥላሴ የሚለው ቃል መጠቀም ስሕተት ነው ከሚሉ ተቺዎች መኻል አንዱ ናቸው።
- "The Oneness of God" በተባለው መጽሐፋቸው እንዲህ ብለዋል፣ "There are severe problems with trinitarian terminology. First, the Bible nowhere uses the word trinity." loc. 2616።
- ጩኸታቸውን ቧልት የሚያደርገው ግን፣ በዚሁ መጽሐፍ "monotheism," "Oneness Pentecostals," "substitute," "millennium," "modalism," "unitarianism," "person" ወዘተ የሚሉትን ቃላት ደጋግመው መጠቀማቸው ነው።

- "monotheism," "modalism," "unitarianism," ወዘተ የነገረ መለኮት ስያሜ እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጠቅሰው የምናገኛቸው ቃላት አይደሉም።
- የነገረ መለኮት ቃል መጠቀም ስሕተት ነው እያሉ፣ መልሰው የነገረ መለኮት ቃል መጠቀም ከራስ ጋር መቃረን ነው።
- ዐሳብ እንዲወክሉ ሙያዊ ቃላትን መጠቀም ቢሆን ጥቅም እንጂ፣ ጉዳት የለውም።
- በመሠረቱ ሙያዎች ሁሉ የራሳቸው የሆነ ሙያዊ ቃላት አላቸው።
- ባይሆን ጊዜ ሰጥተን ልንነጋገርበት የሚገባው ነጥብ፣ "ፅንሰ ዐሳቡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ድጋፍ አለው ወይስ የለውም?" የሚለውን ነው።

## ቁም ነገር

- ሥላሴ የሚለው ቃል የነገረ መለኮት ቃል እንጂ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ስላልሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኘውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ የሚለውን ስያሜ ነው። ስለዚህ ቁም ነገሩ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ስንል ምን ማለት ነው የሚለውን ጉዳይ የሚተነትነው ሥላሴ የሚለው ፅንሰ ዐሳብ ነው። ስለዚህ መነጋገር ያለብን አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው በሚለው ጉዳይ ላይ እንጂ፣ ይህን ስያሜ ለምን ተጠቀማችሁ በሚለው መሆን የለበትም።

## ሥሉሳውያት ምንባባት

- በዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከኀምሳ በላይ ክፍሎች አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን በጥምረት ጠቅሰዋል። እነዚህ ክፍሎች፣ “ሥሉሳውያት ምንባባት” በእንግሊኛው፣ “Triadic Texts” በመባል ይታወቃሉ።

**በአንድ ዐውደ ምንባብ “አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ” የሚሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች**

**ክፍል ፩**

| የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት | ምንባብ | አብ | ወልድ | መንፈስ ቅዱስ |
|---|---|---|---|---|
| ማቴዎስ | 3÷13-17 | ቊ. 17 | ቊ. 16 | ቊ. 16 |
| ሉቃስ | 1÷35 | ቊ. 35 | ቊ. 35 | ቊ. 35 |
| ሐዋርያት ሥራ | 2÷33 | ቊ. 33 | ቊ. 33 | ቊ. 33 |
| ሮሜ | 5÷1-6 | ቊ. 5 | ቊ. 1 | ቊ. 5 |
| | 8÷3-4 | ቊ. 3 | ቊ. 3 | ቊ. 4 |
| | 8-9 | ቊ. 8 | ቊ. 9 | ቊ. 9 |
| | 8÷15-17 | ቊ. 15 | ቊ. 16 | ቊ. 17 |
| | 8÷26-30 | ቊ. 26 | ቊ. 29 | ቊ. 26 |
| | 15÷16 | ቊ. 16 | ቊ. 16 | ቊ. 16 |
| | 15÷30 | ቊ. 30 | ቊ. 30 | ቊ. 30 |
| 1ቆሮንቶስ | 2÷2-5 | ቊ. 5 | ቊ. 2 | ቊ. 4 |
| | 6÷11 | ቊ. 11 | ቊ. 11 | ቊ. 11 |
| 2ቆሮንቶስ | 1÷21 | ቊ. 21 | ቊ. 21 | ቊ. 21 |
| ገላትያ | 3÷1-5 | ቊ. 5 | ቊ. 1 | ቊ. 2 |
| | 4÷4-6 | ቊ. 4 | ቊ. 6 | ቊ. 6 |
| ኤፌሶን | 1÷3-14 | ቊ. 3 | ቊ. 7 | ቊ. 13 |
| | 2÷18 | ቊ. 18 | ቊ. 18 | ቊ. 18 |
| | 2÷19-22 | ቊ. 19 | ቊ. 20 | ቊ. 22 |
| | 3÷16-19 | ቊ. 16 | ቊ. 17 | ቊ. 16 |
| | 4÷5-6 | ቊ. 6 | ቊ. 5 | ቊ. 4 |
| | 5÷18-20 | ቊ. 20 | ቊ. 20 | ቊ. 18 |

# ክፍል ፩

| የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት | ምንባብ | አብ | ወልድ | መንፈስ ቅዱስ |
|---|---|---|---|---|
| ፊልጵስዩስ | 3÷3 | ቍ. 3 | ቍ. 3 | ቍ. 3 |
| 1ተሰሎንቄ | 1÷3-6 | ቍ. 3 | ቍ. 6 | ቍ. 5-6 |
| 2ተሰሎንቄ | 2÷13-14 | ቍ. 13 | ቍ. 14 | ቍ. 13 |
| ቲቶ | 3÷5-7 | ቍ. 5 | ቍ. 6 | ቍ. 5 |
| ዕብራውያን | 9÷14 | ቍ. 14 | ቍ. 14 | ቍ. 14 |
| | 10÷29-30 | ቍ. 30 | ቍ. 29 | ቍ. 29 |
| 1ጴጥሮስ | 1÷2 | ቍ. 2 | ቍ. 2 | ቍ. 2 |
| | 3÷18 | ቍ. 18 | ቍ. 18 | ቍ. 18 |
| | 4÷14 | ቍ. 14 | ቍ. 14 | ቍ. 14 |
| 1ዮሐንስ | 4÷2 | ቍ. 2 | ቍ. 2 | ቍ. 2 |

# አንቀጸ ሃይማኖት

- ቤተ ክርስቲያን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ላይ ያለትን ትምህርት ይፋ ያደረገችው፣ የሮሙ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ክርስትናን መቀበሉን ባበሠረበት (312-337)፣ በግዛቱ ሥር ያሉ አገሮች ክርስትናን እንዲቀበሉ መመሪያ በሰጠበት ወቅት ነው።

- ከዚያ በፊት ሮማውያን በሚገዟቸው አገሮች ክርስትና በሕግ የተወገዘ ሃይማኖት ስለነበር፣ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ማንነት ዙሪያ ውስጥ ለውስጥ ሲብላላ የቈየው የነገረ መለኮት ጥያቄ የሃይማኖት ነጻነቱን ተከትሎ ይፋ ሆነ።

- አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ማን ነው የሚለው ጉዳይ ለስድስት መቶ ዓመታት የትልቅ ውዝግብ ምክንያት ነበር። በኒቂያ 325 ዓ.ም፣ በቊስጥንጥኒያ 381 ዓ.ም፣ በኤፌሶን 431 ዓ.ም፣ በኬልቄዶን 451 ዓ.ም ትልቅ የውይይት አጀንዳ የነበረው፣ ትምህርተ ሥላሴ ነው። እነዚህ አገሮች ሁሉ ዛሬ በቱርክ ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

- በኒቂያና በቊስጥንጥኒያ የወጣውን የሃይማኖት መግለጫ እነሆ



# የኒቅያ የሃይማኖት መግለጫ
# (ኒቅያ ወቍስጥንጥኒያ)

**Niceno-Constantinopolitan Creed**

- ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፣ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ።
- እርሱ ብቻ የአብ ልጅ በሚሆን፣ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ በተወለደ፣ ከአምላክ በተገኘ አምላክ፣ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፣ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፣ በህልውናው ከአብ ጋር አንድ በሆነ፤ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፤ ሁሉ በእርሱ በሆነ፣ ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ ድኅነታችንም ከሰማይ በወረደ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም ሥጋ ነሥቶ ሰው በሆነ፣ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመንም ስለ እኛ በተሰቀለ፤ መከራ በተቀበለ፤ በሞተ፣ በተቀበረም፤ በቅዱሳት መጻሕፍትም እንደ ተጻፈ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣ፣ ወደ ሰማይም በወጣ፣ በአብ ቀኝ በተቀመጠ፣ በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ዳግመኛ በክብር በሚመጣ፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ በሌለው በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ።
- ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለትና በሚከበር፣ ከአብ[ና ከወልድ] በሚሠርጽ፣ በነቢያት በተነገረ፣ የሕይወት ጌታና ሰጪ በሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስም አምናለሁ።
- የሁሉም በሆነች በአንዲት ቅድስት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንም አምናለሁ። ለኀጢአት ማስተስረያ በአንዲት ጥምቀትም አምናለሁ። የሙታንን ትንሣኤና ገና የሚመጣውን ዓለም ሕይወትም እጠባበቃለሁ።

  አሜን።

# Niceno-Constantinopolitan Creed

We believe in one God, the Father Almighty, Maker of heaven and earth, and of all things visible and invisible;
And in one Lord Jesus Christ, the Son of God, the Only-begotten, Begotten of the Father before all ages, Light of Light, Very God of Very God, Begotten, not made; of one essence with the Father; by whom all things were made:
Who for us men and for our salvation came down from heaven, and was incarnate of the Holy Spirit and the Virgin Mary, and was made man;
And was crucified also for us under Pontius Pilate, and suffered and was buried;
And the third day He rose again, according to the Scriptures;
And ascended into heaven, and sits at the right hand of the Father;
And He shall come again with glory to judge the living and the dead, Whose kingdom shall have no end.
And we believe in the Holy Spirit, the Lord, and Giver of Life, Who proceeds from the Father, Who with the Father and the Son together is worshipped and glorified, Who spoke by the Prophets;
And we believe in one, holy, catholic, and apostolic Church.
We acknowledge one Baptism for the remission of sins

Πιστεύομεν εἰς ἕνα Θεὸν Πατέρα παντοκράτορα
ποιητὴν οὐρανοῦ καὶ γῆς ὁρατῶν τε πάντων καὶ ἀοράτων·
καὶ εἰς ἕνα Κύριον Ἰησοῦν Χριστὸν
τὸν υἱὸν τοῦ Θεοῦ τὸν Μονογενῆ,
τὸν ἐκ τοῦ Πατρὸς γεννηθέντα πρὸ πάντων τῶν αἰώνων,
Φῶς ἐκ Φωτός,
Θεὸν ἀληθινὸν ἐκ Θεοῦ ἀληθινοῦ,
γεννηθέντα οὐ ποιηθέντα,
ὁμοούσιον τῷ Πατρί,
δι' οὗ τὰ πάντα ἐγένετο·
τὸν δι' ἡμᾶς τοὺς ἀνθρώπους καὶ διὰ τὴν ἡμετέραν σωτηρίαν
κατελθόντα ἐκ τῶν οὐρανῶν,
καὶ σαρκωθέντα ἐκ Πνεύματος Ἁγίου καὶ Μαρίας τῆς
παρθένου,
καὶ ἐνανθρωπήσαντα,
σταυρωθέντα τε ὑπὲρ ἡμῶν ἐπὶ Ποντίου Πιλάτου,
καὶ παθόντα, καὶ ταφέντα,
καὶ ἀναστάντα τῇ τρίτῃ ἡμέρᾳ κατὰ τὰς γραφὰς,
καὶ ἀνελθόντα εἰς τοὺς οὐρανοὺς,
καὶ καθεζόμενον ἐν δεξιᾷ τοῦ Πατρὸς,
καὶ πάλιν ἐρχόμενον μετὰ δόξης κρῖναι ζῶντας καὶ νεκρούς,
οὗ τῆς βασιλείας οὐκ ἔσται τέλος·
καὶ εἰς τὸ Πνεῦμα τὸ Ἅγιον, τὸ Κύριον καὶ Ζωοποιόν,
τὸ ἐκ τοῦ Πατρὸς ἐκπορευόμενον,
τὸ σὺν Πατρὶ καὶ Υἱῷ συμπροσκυνούμενον καὶ
συνδοξαζόμενον,
τὸ λαλῆσαν διὰ τῶν προφητῶν·
εἰς μίαν ἁγίαν καθολικὴν καὶ ἀποστολικὴν ἐκκλησίαν·
ὁμολογοῦμεν ἓν βάπτισμα εἰς ἄφεσιν ἁμαρτιῶν·
προσδοκῶμεν ἀνάστασιν νεκρῶν



# ጸሎተ ሃይማኖት

- ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ዋሕድ ዘህልው ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም።
- በርሃን ዘእምብርሃን አምላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን። ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ። ዘቦቱ ኵሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ።
- ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድኀኒትነ ወረደ እምሰማያት ተሰብአ ወተሰገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል ኮነ ብእዚ ወተሰቅለ በእንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ። ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት ዐረገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማኑ አቡሁ፤ ዳግመ ይምጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ወአልቦ ማኅለቅተ ለምንግሥቱ።
- ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እምአብ ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለአብ ወወልድ ወነበበ በነቢያት። ወነአምን በአሐቲ ቅዲስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት። ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኀጢአት ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለም ዓለም።

# የአስተምህሮው መሠረታውያኑ ጭብጦች

፩. አንድ አምላክ ብቻ አለ።

፪. አብ አምላክ ነው።

፫. ወልድ አምላክ ነው።

፬. መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው።

፭. አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት ናቸው።

እነዚህን መሠረታውያን ጭብጦች በሌላ መንገድ ስንገልጻቸው:—

1) አብ አምላክ ነው፤ ወልድ አምላክ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው።

2) አብ ወልድ አይደለም፤ ወልድም መንፈስ ቅዱስ አይደለም፤ መንፈስ ቅዱስም አብ አይደለም።

3) አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ።

# የጉዞ መስመር

- የትምህርተ ሥላሴን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ለማጽናት፣
  - በወዲህ ኢየሱስ አምላክ አይደለም ለሚሉ አርዮሳውያን ምላሽ መስጠት፣
  - በወዲያም አብና ወልድ የተለያዩ አካላት አይደሉም ለሚሉ ሰባልዮሳውያን ዐጸፋ መሰንዘር ነው።
- እንግዲያው ትምህርተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ለማጽናት፣ የምንሄደው በሚከተሉት ሁለት ዐቢይ ጐዳናዎች ነው።
  - አንድም የወልድን አምላክነት ማሳየት።
  - ሁለትም አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን
  - ማጽናት።



# ዐቢይ ተፋልሶዎች የኑፋቄዎቹ ሥረ መሠረት

- ይህ የሥላሴአውያን መሠረተ እምነት ይሆኑን እንጂ፣ በቤተ ክርስቲያን የታዩ ኑፋቄዎች በደምሳሳው በሁለት ዐቢይ ወገን የሚከፈሉ ናቸው።
- አንደኛው፤ አርዮሳዊነት የሚባለው ሲሆን ሌላው ደግሞ ሰባልዮሳዊነት የሚባለው ነው።
- አርዮሳውያን ወልድ አምላክ ነው እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው የሚለውን መሠረተ እምነት ወግድ ሲሉ፣
- ሰባልዮሳውያን ደግሞ ቊጥር አንድን እንቀበላለን ነገር ግን አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት ናቸው የሚለው ስሕተት ነው ባይ ናቸው።
- ዛሬ የአርዮሳውያኑን ትምህርት የሚያስተምረው የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀው አሜሪካዊው ድርጅት ሲሆን፣
- የዛሬዎቹ ሰባልዮሳውያን ደግሞ "United Pentecostal Church International" የሚባለው ድርጅት ነው።
- እነዚህ ሁለት መናፍቃውያን ዐስተሳሰቦች ጥንታውያን ቢሆኑም፣ ዐፈር ልሰው የተነሡት ግን በዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ በአገረ አሜሪካ ነው።

# ውጉዝ ከመ አርዮስ

## የአርዮሳዊነት ዐበይት ዐዋጆች

1. ኢየሱስ ዘላለማዊ አይደለም።
   - “ያልነበረበት ዘመን ነበር”።
   - “There was [a time] when He was not.” “ἦν ποτε ὅτε οὐκ ἦν” — “ኢን ፖቴ ኦቴ ኡክ ኢን”።
2. ኢየሱስ ፍጡር ነው።
   - የተፈጠረ እንጂ የተወለደ አይደለም።
   - He is γενητός (made), not ἀγέννητος (unbegotten).
3. ኢየሱስ “አምላክ” ሊባል የሚችለው፣ በእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ፣ በባሕርይ/በኑባሬ አይደለም።
4. ኢየሱስ በባሕርይ ከአብ ያንሳል (ontologically inferior)።
   - ከአብ ጋር ተመሳሳይ ባሕርይ (essence--οὐσία) የለውም።
5. ኢየሱስ ከአብ ጋር አንድ ባሕርይ (ὁμοούσιος) ያለው ሳይሆን፣ የተለየ ባሕርይ ἑτεροούσιος (“of different essence”) ያለው ነው።
   - አንድ ዐይነት ባሕርይ ὁμοούσιος ሳይሆን፣ (ኒቂያ ከአብ ጋር አንድ ባሕርይ አለው ὁμοούσιος τῷ Πατρί ይላል)።
     - ✓ ὁμο- (homo) = “same.”
     - ✓ οὐσία (ousia) = “essence,” “substance,” “being.”
     - ✓ ὁμοούσιος = “of the same essence/substance.”
   - ግሚስ አርዮሳውያን (Semi-Arianism) ከአብ የተለየ ኑባሬ ἑτεροούσιος (“of different essence”) አለው የሚለውን በማሻሻል ሆሞዮስዮስ ነው ὁμοιούσιος (“of similar essence”) ለማለት ቢሞክሩም፣ ቤተ ክርስቲያን ግን ይህንንም ዐሳብ ኑፋቄ ብላዋለች።
   - በአጠቃላይ ሆሙሲዮስ (ὁμοούσιος) ርቱዕ ሃይማኖት ሲሆን፣ ሄትሮሲዮስና ἑτεροούσιος፣ ሆሞዮስዮስ (ὁμοιούσιος) ደግሞ አርዮሳዊነትና ግሚስ አርዮሳዊነት ነው።

# ውጉዝ ከመ ሰባልዮስ

## የሰባልዮሳዊነት ዐበይት ዐዋጆች

1. አስተምህሮው ስያሜውን ያገኘው ከሰባልዮስ ነው። ሮም የተማረ ሊቢያዊ ቄስ 215 ዓ. ም አካባቢ።
2. አስተምህሮው በትልልቆቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ተኰንኗል። ለምሳሌ ጠርጡሊያኖስ፣ ሂፖሊተስ፣ አትናቴዎስ።
3. የአስተምህሮው ማዕከል አንድ አካል ሦስት መገለጦች የሚል ነው። አንዱ አምላክ ራሱን በሦስት መንገዶች ገልጾአል። አንድ ተዋናይ የተለያየ ጭንብሎች አድርጎ በተለያየ ማንነት ራሱን እንደሚገልጸው ሁሉ፣ አብም ራሱን በተለያየ መንገድ አንደ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ገልጾአል ባይ ነው።
4. አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት ናቸው የሚለው ትምህርት ስሕተት ነው ባይ ነው።
5. በዛሬ ጊዜ በዓለም ላይ ይህን አስተምህሮ በስፋት የሚያስተምረው ድርጅት UPCI በመባል ይታወቃል። የኢትዮጵያውን ድርጅት የቈረቈረው ይህ አሜሪካዊ ተቋም ሲሆን፣ ሕጋዊ ስያሜአቸው የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ይባላል።

# የክርስትና

# መሠረታውያኑ

# ዐዋጆች



# ሀ. እግዚአብሔር ብቻ አምላክ ነው

1) እግዚአብሔር አንድ ብቻ ነው (አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ)

ዘዳ. 4÷35:39፤ 32÷39፤ 2ሳሙ. 22÷32፤ ኢሳ. 37÷20፤ 43÷10፤ 4468፤ 1ቆሮ. 8÷4-6፤ ገላ. 3÷20፤ ያዕ. 2÷19።

2) እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም (በአነዋወሩ/በባሕርዮቱ)።

መዝ. 86÷8፤ ኢሳ. 40÷18:25፤ 44÷7፤ ኤር. 10÷6-7።

3) "እንደ እግዚአብሔር መሆን" የሚለው ውሸት ከሰይጣን ከዲያብሎስ የተገኘ፣ የወንጀሎች ሁሉ አውራ ወንጀል ነው። ዘፍ. 3÷5፤ ኢሳ. 14÷14፤ ዮሐ. 8÷44።

4) “በልዑል እመሰላለሁ” ያለው ሰይጣን ዘላለማዊ ውድቀትን እንጂ፣ አምላክ መሆንን አላገኘም ኢሳ. 14፥14።

ሀ. ሰይጣን አምላክ ሳይሆን፣ የውሸት አምላክ ወይም የዚህ ዓለም አምላክ ነው 2ቆሮ. 4፥4።

ለ. ዕብራውያን 2፥7 መላእክትን አማልክት ቢልም ከዕብራውያን 1 እና 2 ዐውደ ምንባብ አንጻር እነዚህ መላእክት ትክክል ባልሆነ ሁኔታ ራሳቸውን ከክርስቶስ በላይ ያደረጉ ናቸው።

ሐ. በቅዱሳት መጻሕፍት መላእክትን እንደ አማልክት ወይም እንደ አማልክት ልጆች የሚገልጹ ከሆነ፣ እየገለጿቸው ያለው እንደ ሐሰተኛ አማልክት ነው። መዝሙር 29፥1፤ 86፥8-10፤ 89፥6፤95፥3፤ 96፥4-5፤ 97፥7-9።

5) “እንደ እግዚአብሔር እሆናለሁ” ሲል የተንጠራራው ሰው በራሱ ላይ ያመጣው ክፋውንና ደጉን ማወቅ እንጂ እግዚአብሔርን መሆን አልነበረም ዘፍ. 3÷22።

ሀ. ሰዎች “እግዚአብሔርን ይመስላሉ” ወይም “አምሳለ መለኮት ናቸው” የተባለው የእግዚአብሔርን ግብረገባዊ ባሕርይ ተካፋይ መሆናቸውን ለማመልከት እንጂ ሰዎች አማልክት ናቸው ለማለት አይደለም። ዘፍ. 1÷26-27፤ 5÷1፤ 1ቆሮ. 11÷7፤ ኤፌ. 4÷24፤ቈላ. 3÷10።

ለ. “ክርስቶስን መምሰል” የሚለው ሐረግ እንደ ዐውደ ምንባቡ የሚከተሉትን ሁለት ትርጒሞች ብቻ የሚወክል ነው

1. የግብረገባዊ ባሕርይው ተካፋይ መሆን 1ዮሐ. 3÷2፤ ሮሜ 8÷29።

2. እንደ ክርስቶስ በማይሞትና በከበረ የትንሣኤ አካል ከሙታን መነሣትን ፊልጵ. 3÷21፤ 1ቆሮ. 15÷49።

ሐ. “የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ” መሆን ማለት፣ ግብረጋባዊ ባሕርይን አመልካች ነው። “ከክፉ ምኞት የተነሣ በዓለም ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት አምልጣችሁ ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች እንድትሆኑ በእነዚህ ነገሮች አማካይነት እጅግ ታላቅና ክብር የሆነውን ተስፋ ሰጥቶናል” 2ጴጥ. 1÷4፤ መካፈል የሚለውን የቃል ትርጒም ለመመርመር የሚከተሉትን ምንባባት ይመለከቷል ዕብ. 12÷10፤ 1ቆሮ. 10÷18:20። 2ቆሮ. 1÷17፤ 1ጴጥ. 5÷1።

መ. ሙሴ፣ “እንደ እግዚአብሔር” ወይም “በእግዚአብሔር ፋንታ” ነበር እንጂ፣ እግዚአብሔር አልነበረም ዘፀ. 4÷16፤ 7÷1።

ሠ. ታላላቅ ወይም እጅግ ከፍ ያሉ ሰዎች አማልከት አይደሉም ሕዝ. 28÷2:9፤ ኢሳ. 31÷3፤ 2ተሰሎ. 2÷4።

ረ. አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቅጆች፣ ሕዝቅኤል 32÷21፤ ተዋጊዎችን ወይም ወታደሮችን፣ “ኀያላን አማልክት” (“mighty gods”) ብለዋቸዋል። ነገር ግን ከዐውደ ምንባቡ በግልጽ የምንማረው፣ ይህ ዐይነቱ ስያሜ የተሰጣቸው እግዚአብሔርን በማያውቁ አረማውያን/አሕዛብ መንግሥታት እንጂ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ (በእስራኤላውያን ዘንድ) አልነበረም፤ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ሕዝ 28÷2:9።

ሰ. በኦሪት ወንጀል የሠራ ሰው የሚቈመው በእግዚአብሔር ፊት እንጂ በዳኞች ፊት አይደለም። ዳኞቹ ሢመት ከአምላክ የተገኘ ስለሆነ፣ በዳኞቹ ፊት መቈም በአምላክ (በዕብራይስጥ ኤሎሂም אֱלֹהִים ፊት መቈም ነው) ዘፀ. 22÷8:9:28 ከዘዳ. 19÷17 ጋር ያነጻጽሯል።

ሸ. በመዝሙር 82 ላይ አማልክት (በዕብራይስጥ ኤሎሂም אֱלֹהִים) የሚለው ቃል፣ ቅን ያልሆነ ፍርድ የሚበይኑትን የእስራኤል ግፈኛ ዳኞችን በምፀት የሚሸነቍጥ ምንባብ እንጂ፣ ሰዎች አማልክት ናቸው ለማለት አይደለም። ስለዚህ ፈራጆቹን ኤሎሂም ያላቸው በምፀት መልክ ነው። በቀጥታ “አማልክት ናችሁ”፣ “የልዑል እግዚአብሔር ልጆች ናችሁ” (ቍ. 6) አላለም።

6) አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ ካለ፣ አማልክት የተባሉት ሁሉ እውነተኛ አምላክት አይደሉም ዘዳ. 32÷21፤ 1ሳሙ. 12÷21፤ መዝ. 96÷5፤ ኢሳ. 37÷19፤ 1ቆሮ. 8÷4፤ 10÷1920።

7) አማልክት የተባሉት ሁሉ፣ ከሐሰተታ አምልኮዎች ጀርባ የሚሠሩ አጋንንት ናቸው እንጂ ዘዳ. 32÷17፤ መዝ. 106÷37፤ 1ቆሮ. 10÷20፤ ገላ. 4÷8።

## ለ. ኢየሱስ አምላክ (እግዚአብሔር) ነው

### 1)ታላቅ አምላክ (ኤልጊቦር אֵל גִּבּוֹר) ተብሏል፤ ኢሳ. 9÷6።

አንዳንድ ኀያሲያን ኢየሱስ፣ “ታላቅ አምላክ” (ዕብራይስጥ ኤልጊቦር אֵל גִּבּוֹר) እንጂ፣ “ሁሉን ቻይ አምላክ” (ኤል ሻዳይ אֵל שַׁדַּי) (ግሪክ ፓንቶክራቶ παντοκράτωρ) አልተባለም የሚል ክርክር ያነሣሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ “ኀያል አምላክ” እና “ሁሉን ቻይ አምላክ” በሚለው ገለጻ ውስጥ አንዳችም የትርጒም ልዩነት የለም።

- ምክንያቱም አብ ራሱ ኀያል አምላክ ተብሏል፤ ኢሳ. 10÷21፤ 2ቆሮ. 6÷18። ሁለቱ የማዕረግ ስሞች የሚበላለጡ ቢሆን ኖሮ አምላክ ባነሰው ስም አይጠራም ነበር።
- እንዲሁም አብ ሁሉን ቻይ አምላክ ተብሏል፤ ራእ. 21÷22፤ 19÷6:15።
- ወልድ ሁሉን ቻይ አምላክ ተብሏል፤ ራእ. 1÷8-18፤ 22÷12-13።
- “ኤል” (אֵאֵל) ማለት፣ “አምላክ” ማለት ነው።
- አብና ወልድ አምላክ ሆነው፣ የመበላለጥና የመቀዳደም ልዩነት ካላቸው ሁለት አማልክት ናቸው ማለት ነው። ይህ ጣዖት አምልኮ ነው፤ የመድብለ አማልክት ዐስተሳሰብ ነው።

## 2)ኢየሱስ “እግዚአብሔር” ተብሏል፤ ዮሐ. 1÷1።

አንዳንዶች ይህን ክፍል “a god” ብለው ተርጉመውታል። ይህም ከአብ እንደሚያንስ በሚያሳይ መልኩ። ይህ ግን ስሕተት ነው።

- ተመሳሳይ የሰዋስው አወቃቀር ያላቸው ክፍሎች ላይ እግዚአብሔር የሚለውን ቃል “a god” ብለው አልተረጎሙም ማር. 12÷27፤ ሉቃ. 20÷38፤ ዮሐ. 8÷54፤ ፊልጵ. 2÷13፤ ዕብራውያን 11÷16።
- እግዚአብሔር በሚለው የግሪክ ቃል ፊት ውስን መስተኣምር መኖርም ሆነ አለመኖር አንዳችም የትርጉም ልዩነት አያመጣም። በዚሁ ዐውድ ዮሐ. 1÷6:12:13:18 የመለከቷል። ማር. 12÷27፤ ሉቃ. 20÷37-38፤ ዮሐንስ 3÷2፤ 13÷3፤ ሮሜ 1÷21፤ 1ተሰ. 1÷9፤ ዕብ. 9÷14፤ 1ጴጥ. 4÷10-11።

## 3) ኢየሱስ “እግዚአብሔር ወልድ” (μονογενὴς θεὸς) ተብሏል፤ ዮሐ. 1፥18።

- ነባሩ ትርጉም አሳስቶ ቢተረጉመውም፣ የይሖዋ ምስክሮችን ጨምሮ ሁሉም የዐማርኛ ትርጉሞች ጥንታውያኑን ዕደ ክታባት መሠረት በማድረግ፣ “አንድያ ልጁ የሆነው አምላክ” ብለዋል።
- ቢሆንም “የይሖዋ ምስክሮቹ” ትርጉም ነገሩን በማሳሳት፣ ኢየሱስን በሚያመለክተው አምላክ ላይ “a god” ብሏል። ለዚህ ክሕደት አንዳችም የሰዋስው ወይም የዐውድ ማስረጃ አላቀረበም።

# 4)“ኢየሱስ አምላኬና ጌታዬ” ተብሏል፤ ዮሐ. 20፥28።

አንዳንድ ኀያስያን፣ “አምላኬ” የተባለው አብ ነው፣ “ጌታዬ” የተባለው ኢየሱስ ነው የሚል የክርክር ነጥብ ያቀርባሉ (Ὁ κύριός μου καὶ ὁ θεός μου)። ይህ ስሕተት ነው።

- ተመሳሳይ አወቃቀር ያላቸው ሌሎች ክፍሎች አንድን አካል በሚያሳይ መልክ ግልጋሎት ላይ ውለዋል፤ የይሖዋ ምስክሮችን ትርጒም ጨምሮ።
  - “ὁ κύριος καὶ ὁ θεὸς ἡμῶν” ራእይ 4፥11፤
  - “ὁ θεός μου καὶ ὁ κύριός μου” መዝሙር 35፥23።
- “ቶማስ በመደነቅ ወደ አብ መጮኹን አመልካች ነው” የሚለውም ስሕተት ነው። አይሁዳውያን በሚደነቁበት ወቅት የአምላክን ስም የመጥራት ልማድ አልነበራቸውም፤ የላቸውምም። የሕጉ መጽሐፍ፣ “የአምላክህን የእግዚአብሔር ስም በከንቱ አትጥራ” ይላልና።

## 5) ከአባቶች በሥጋ የተወለደው ኢየሱስ ነው። "እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ (θεὸς) ነው፤ አሜን" ሮሜ 9÷5።

- አምላክ ወይም እግዚአብሔር የተባለው ማንን ነው በሚለው ጉዳይ ላይ የመስኩ ምሁራን የተለያየ አስተያየት አላቸው። አንዳንዶች ኢየሱስን ያሳያል ሲሉ አንዳንዶች ደግሞ አብን አመልካች ነው ባዮች ናቸው። "እርሱም" (ὁ ὢν) የሚለው ቃል በስም ሙያ (Nominative case) የቀረበ ስለሆነ፣ ኋላ ተከትሎ የቀረበው ማሰሪያ አንቀጽ፣ ከአባቶች በሥጋ መጣ የተባለውን አካል ማለትም ክርስቶስን አመልካች ነው።
- ከዚህ በተጨማሪ በዐረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ ድንገተኛ የሆነ የስም ለውጥ በማድረግ፣ ክፍሉ አብን ያሳያል ማለት ሲበዛ አዳጋች ነው። በበርካታ ግልጽ ምንባባት ውስጥ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስን አምላክ ስላለው በዚህ ቦታ አምላክ አይለውም ብሎ ማሰብ አይቻልም ሮሜ 10÷13፤ ፊልጵ. 2÷6፤ ቲቶ 2÷13።

## 6)“ይህም የተባረከ ተስፋችን የሆነውን የታላቁን የአምላካችንንና የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ በመጠባበቅ ነው” ቲቶ 2፥13።

- በክፍሉ ውስጥ ኢየሱስ አምላክ አልተባለም የሚሉ ሰዎች አሉ። ይሁን እንጂ ይህ ዐይነቱ ትምህርት ከክፍሉ የሰዋስው አወቃቀርም ሆነ ዐውዳዊ ትርጉም ጋር ይቃረናል።
- ዐውዳዊ ትርጉም። አንደኛ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ በኤፌሶን ሰዎች “የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት” እያሉ አረማዊ አምልኮ ያደርጉ ነበር (ሐሥ. 19፥28-34)። እንዲሁም በዘመኑ የነበሩ ነገሥታት፣ይል ራሳቸውን እንደ አምላክ ይመለከተ እንደ ነበር ታሪክ ይነግረናል። ለምሳሌ የግሪኩ ንጉሥ አንትዮከስ ኢጲፋኒዮስ (Antiochus Epiphanes) ራሱን፣ “የአምላክ መገለጥ” ይል እንደ ነበር ይታወቃል። ቀዳማዊ በጥለሚዮስ (Ptolemy I) ራሱን “መድኀኒትና አምላክ” ይል እንደ ነበር ይነገራል። ዩሉዮስ ቄሳር (Julius Caesar) አምላክና መድኀኒት ይባል ነበር። በዚህ ዐውድ ውስጥ ሐዋርያው እውነተኛ አምልኮ ለክርስቶስ ኢየሱስ መሰጠት አለበት በታላቁ አምላክና መድኀኒት ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለውን ቅጽል ለክርስቶስ ኢየሱስ አይጠቀምም ባለት አይቻልም።
- **ሁለተኛ፤** ጳውሎስ መገለጥ (“ኢፒፋንያ” ἐπιφάνειαν) የሚለውን ቃል የሚጠቀመው፣ ከክርስቶስ ጋር በተያያዘ መንገድ ነው (2ተሰ. 2፥8፤ 1ጢሞ. 6፥14፤ 2ጢሞ. 1፥10፤ 4፥1:8)።
- **ሦስተኛ፤** እግዚአብሔር ከሚለው ስም ፊት ያለው ቅጽል ማለትም “ታላቅ” (μεγάλου) አብን በሚያሳይ መልክ፣ ግልጋሎት ላይ የዋለበት የዐዲስ ኪዳን ክፍል የለም።

## ሰዋስዋዊ ትርጕም

ሻርፐስ በመባል የሚታወቀው የግሪክ ሰዋስው ሕግ፣ ተመሳሳይ ሙያ ያላቸው ከሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ስሞች በእና ተያይዘው በአንደኛው ስም ላይ ውስን መስተኣምር ኖሮ ሁለተኛው ላይ ውስን መስተኣምር ከሌለ፣ ሁለቱም ስሞች አንድን አካል የሚያመለክቱ ናቸው (τοῦ μεγάλου θεοῦ καὶ σωτῆρος ἡμῶν Ἰησοῦ Χριστοῦ)። ይህ ዐይነት የሰዋስው አወቃቀር ካላቸው ክፍሎች መኻል የሚከተሉትን ምንባባት ይመለከቷል:— ሉቃ. 20÷37 (τὸν θεὸν Ἀβραὰμ καὶ θεὸν Ἰσαὰκ καὶ θεὸν Ἰακώβ)፤ ራእ. 1÷6 (τῷ θεῷ καὶ πατρὶ αὐτοῦ)።

**7)“በአምላካችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ፣ የክብር እምነት ላገኙ” 2ጴጥ. 1÷1።**

- ይህ ከቲቶ 1÷1 ጋር ተመሳሳይ የሰዋስው አወቃቀር ያለው ክፍል ነው። ከዚህ ጋር ተዛማጅ የሆኑ የሰዋስው አወቃቀር ያላቸውን ሌሎች ክፍሎች ይመለከቷል:— 2ጴጥ. 1÷11፤ 2÷20፤ 3÷2:18።

**8)“የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መጣ፣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተታም በሆነው በእርሱ አለን፤ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተታ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው” 1ዮሐ. 5÷20።**

- “በእርሱም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ ክርስቶስን ከሆነ፣ የዘላለም ሕይወት የሚለውም ሐረግ ክርስቶስን የሚያመለክት ነው። እርሱም እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።

# የአስተምህሮው መሠረታውያኑ ጭብጦች

፩. አንድ አምላክ ብቻ አለ።

፪. አብ አምላክ ነው።

፫. ወልድ አምላክ ነው።

፬. መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው።

፭. አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት ናቸው።

## ሐ. ኢየሱስ ያህዌ ተብሏል

- “ያህዌ” የሚለው ስም የዕብራይስጥ ስም መሆኑን ልብ ይሏል። ዐዲስ ኪዳንም ሆነ ወደ ግሪክ በተተረጐመው የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም፣ “ያህዌ” የሚለውን የዕብራይስጥ ስም እንዲሁም ማናቸውም ዐይነት የዕብራይስጥ ስሞችን አንድ ጊዜ እንኳ አልተጠቀሙም። የዐዲስ ኪዳን ጸሐፍያን ብሉያትን በጠቀሱባቸው ቦታዎች ላይ፣ “ያህዌ” የሚለውን የዕብራይስጥ ስም፣ “ጌታ” (ግሪክ “ኩርዮስ”) በሚለው ስም ነው የተኩት።

- በብሉይ ኪዳን ስለ ያህዌ የተጠቀሱ ምንባባት፣ በዐዲስ ኪዳን ኢየሱስን ያመለከቱባቸው እጅግ በርካታ ምንባባት አሉ። ከእዚህ የምንማረው ሐቅ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ መባሉን ነው።
- ጥቂት አስረጆችን እነሆ 1ጴጥሮስ 2÷3-4 በቀጥታ የተወሰደው ከመዝሙር 34÷8 ላይ ነው። በክፍሉም ጌታ የተባለው ያህዌ ነው። 1ጴጥሮስ 3÷14-15 ያለው ክፍል የተወሰደው ከኢሳይያስ 8÷12-13 ላይ ነው።

- ኢዮኤል 2፥32፣ “የያህዌን ስም የሚጠራ ይድናል” ሲል፣ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ይህን ክፍል ጠቅሶ፣ “የጌታን ስም የሚጠራ ይድናል” ሮሜ 10፥13 ይለናል። ዕብራይስጡ ያህዌ የሚለውን የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ጌታ እንደሚለው ልብ ይሏል።

- በብሉያት ያህዌ መልእክተኛውን በፊቱ እንደሚልክ፣ መልእክተኛውም ፊት ፊቱ እየሄደ መንገድን እንደሚያዘጋጅለት ይናገራል። ዐዲስ ኪዳን ይህ መንገድ ጠራጊ መጥምቁ ዮሐንስ እንደ ሆነ ይገልጻል። ይህ ማለት መንገድ ጠራጊውን ተከትሎ የመጣው ኢየሱስ ያህዌ ነው ኢሳ. 40፥3፤ ማቴ. 3፥3፤ ማር. 1፥3፤ ዮሐ. 1፥23።

- በብሉይ ያህዌ ቤተ መቅደስና የማሰናከያው ዐለት እንደ ሆነ ይገልጻል። ጴጥሮስ ይህን ክፍል በቀጥታ በመጥቀስ፣ ኢየሱስ ቤተ መቅደሱና የማሰናከያው ዐለት እንደ ሆነ ገልጾአል። ኢሳ. 8፥13-14፤ 1ጴጥ. 2፥7-8።

- ብሉያት ጒልበት ሁሉ የሚንበረከክልት አንደበት ሁሉ የሚያውጅለት ያህዌ እንደ ሆነ ሲገልጽ፣ ጳውሎስ ይህን ክፍል በመጥቀስ ጒልበት ሁሉ የሚነበረከክለት አንደበት ሁሉ የሚያውጅለት ኢየሱስ እንደ ሆነ አስተምሯል ኢሳ. 45፥23፤ ፊልጵ. 2፥10-11።

## መ. ከአብ ጋር ትክክል ነው

- ፊልጵስዩስ 2÷5-11 ለነገረ ክርስቶስ እጅግ ወሳኝ ከሚባሉ ምንባባት መኻል አንዱ ነው። ይህ ክፍል ከጳውሎስ በፊት የነበረ መዝሙር እንደ ሆነ ይታሰባል (ክፍሉ በግጥም መልክ ስለቀረበ)። ግጥም መሆኑ በሁሉ ዘንድ ቢታመንም፣ አንዳንድ ለዘብተኛ ሊቃውንትት፣ ከጳውሎስ በፊት ቤተ ክርስቲያን ትዘምረው የነበረ መዝሙር ነው የሚለውን ጉዳይ አይቀበሉም። ሐዋርያው ጳውሎስ የፊልጵስዩስን መልእክት ሮም ሆኖ እንደ ጻፈው የነገራል (55 ዓ.ም እስከ 62 ዓ.ም ባለው ጊዜ)። ይህ ክፍል ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት አምላክ እንደ ነበረ፣ ራሱን እጅግ ዝቅ ዝቅ በማድረግ ሰው እንደ ሆነ፤ እንዲያውም ለመስቀል ሞት እንኳ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ ያስተምራል (ቍ. 5-8)። በትንሣኤው ጊዜ እግዚአብሔር ከፍጥረት ሁሉ በላይ እጅግ ከፍ ከፍ በማድረግ፣ የፍጥረት ሁሉ ባለቤት መሆኑን እንዳረጋገጠለት ይናገራል (ቍ. 9-11)።

- እንደ፣ “ይሖዋ ምስክር” ያሉ መናፍቃን ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት እንደ ነበረ ይስማማሉ። ነገር ግን ሰው ሆኖ ከመምጣቱ በፊት፣ ሊቀ መልአክ ሚካኤል ነበር የሚል ዐሳብ አላቸው። “በእግዚአብሔር መልክ” የሚለውን ዐሳብ አምላክ መንፈስ እንደ ሆነው ሁሉ፣ ኢየሱስም መንፈስ መሆኑን የሚገልጽ ነው ባዮች ናቸው። “መተካከል” የሚለውን ዐሳብ፣ አንዳችም ማብራሪያ ሳይሰጡ ባለየ ያልፉታል። “ኦንሊ ጂሰሶቹ” ደግሞ፣ “በእግዚአብሔር መልክ” የሚለውን ዐሳብ፣ ኢየሱስ የአምላክ ቊሳዊ ሽፋን እንዲሆን የተፈጠረ ሥጋና ዐጥንት ነው ሲሉ፣ “መተካከል” ለሚለው ማብራሪያ አይሰጡበትም።

- አንዳንድ ሰዎች የክፍሉ ዐውድ ከቊጥር አንድ ይጀምራል የሚለውን አይቀበሉም፤ ይልቁንም ከቊጥር 5 የጀመረ ዐሳብ አድርገው ይወስዱታል። ለዚህ ክሕደት ዋነኛው ምክንያት ከቊጥር አንድ ጀምሮ ያለው ክፍል ሰዎች እርስ በርስ መከባበር እንዳለባቸው ለማስተማር፣ እንደ ናሙና የቀረበው ዐሳብ በአብና በወልድ መኻል ያለው መከባበር ነው። ዐውዱ ከቊጥር 1 ለመጀመሩ የቃላት ምስስሉን እነሆ:— “የነበረ ሀሳብ” (φρονῆτε ቊ. 2 እና 5)፤ “መቊጠር” (φρονέω ቊ. 3 እና 6)፤ “ትሕትና” (ταπεινόω ቊ. 3 እና 8)። መከባበርን ለማስተማር የክርስቶስና የአብ ጉዳይ በናሙናነት መቅረቡ፣ አብና ወልድ ባሕርያዊ አንድነት ያላቸው መሆኑን አስተማሪ ነው።

- “መቀማት” የሚለውን ቃል “ኢየሱስ የአብን አምላክነት መቀማት አልፈለገም” ይህም አምላክ አለመሆኑን አመልካች ነው ይላሉ (ቊ. 6)። አንደኛ፤ በነባሩ ትርጒም “መቀማት” ብሎ የተረጐመው ቃል (“አርፓገሞን” ἁρπαγμὸν ይህ ቃል በዐዲስ ኪዳን በዚህ ቦታ ላይ ብቻ የሚገኝ ነው (hapax legomena)። ይህ ጒዳይ የመስኩ ምሁራን ቃሉን በምን መልኩ እንተርጒመው በሚለው ጒዳይ ግራ መጋባታቸውን ገለጸዋል)፣ “ጽንቶ መያዝን” አመልካች እንጂ፣ መዝረፍን ወይም መቀማትን ወይም ደግሞ የሌለውን ነገር ለማግኘት መፈለግን (መዝረፍን) አመልካች አይደለም (ዐዲሱ መደበኛ ትርጒም፣ “ሊለቀቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም” ይለዋል)። ሁለተኛ፤ ቀጣዩ ሐረግ (ቊ. 7) መዝረፍን ሳይሆን፣ የሙጥኝ ብሎ መያዝን አመልካች ነው። “ራሱን ባዶ አደረገ” የሚለው ሐረግ፣ እኩልነቱን የሙጥኝ (ሙጭጭ) ብሎ እንዳልያዘ፣ ነገር ግን በትሕትና ራሱን ዝቅ እንዳደረገ (functional subordination) አመልካች ነው። የተለያዩ የእንግሊዝኛ ትርጒሞች፣ ይህን ክፍል በምን ያህል ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደ ተረጐሙት ይመለከቷል።

- “ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን” (ἴσα θεῷ) የሚለው ሐረግ፣ ንጽጽርን ማሳየቱን ልብ ይሏል። ኢየሱስ ከአብ ጋር መተካከሉን። “መተካከል” የሚለው ቃል፣ “ኢየሱስና አብ አንድ አካል ናቸው” (አኃዛዊ አንድነት አላቸው) የሚለውን፣ “የኦንሊ ጂሰስን” ኑፋቄ እንዲሁም “ኢየሱስ ከአብ ያንሳል የሚለውን የይሖዋ ምስክሮች” ትምህርት ይቃወማል። በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ የሚለው ሐረግ ፍጹም አምላክ መሆኑን የሚያመለክት ከሆነ፣ የባሪያውን መልክ ያዘ የሚለውም ፍጹም ሰው መሆኑን አያመለክትም ማለት ነው። ነገር ግን ፍጹም ሰው መሆኑ ቅቡል ከሆነ፣ ፍጹም አምላክ መሆኑም ተቀባይነት ማግኘት ይኖርበታል። ምክንያቱም፣ “የእግዚአብሔር መልክ” (μορφῇ θεοῦ) እና “የባርያውን መልክ” (μορφὴν δούλου) የሚሉት ቃላት፣ ተነጻጽረው እንደ ቀረቡ ልብ ይሏል። ሌላው “ሲኖር ሳለ” (ሂፓርኮን ὑπάρχων) የሚለው ቃል ቋሚ ባሕርይን በሚያሳይ መልክ (present active participle) የቀረበ ነው። በአንጻሩ ባዶ አደረገ፣ ወሰደ፣ ሆነ፣ ተገኘ፣ ትሑት ሆነ፣ ወዘተ የሚሉት ቃላት (aorist verb—time undefined action) መቅረቡ ባሕርዮትን አመልካች ነው እንድንል ያደርገናል።

- ራሱን ባዶ አደረገ (ኬኖ κενόω) ማለት፣ አምላክነቱን ተወ ማለት ሳይሆን፣ ሰውነትን ጨመረ ማለት ነው። ምክንያቱም ክፍሉ ኑባሬውን (አምላክ መሆኑን) መተውን ሳይሆን፣ ሌላ ኑባሬ (ሰው መሆንን) መጨመሩን አመልካች ነውና። ሰው ሰው በመሆን ዝቅ አይልም፤ አምላክ ሰው በመሆን ግን ያለልክ ራሱን ዝቅ አድርጓል። ዝቅታው ሦስት ደረጃ ደረጃ አለው። አንደኛው፤ ከአምላክ ጋር መተካከል ተወ። ሁለተኛው፤ ሰው ሆነ። ሦስተኛው፤ ለመስቀል ሞት ራሱን ዐሳልፎ ሰጠ።

## መ. ስግደትን ተቀብሏል

- አብ ስግደትን በተቀበለበት አግባብ፣ ኢየሱስ ክርስቶስም ስግደትን እንደ ተቀበለ የሚገለጹ በርካታ ምንባባት አሉ። ኢየሱስ ከሰዎች፣ ከመላእክት፣ ከአራቱ ልዩ ፍጥረታት፣ ከሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በአጠቃላይ ጉልበት ሁሉ እንደ እንደ ተንበረከከለት፣ ፍጥረት ሁሉ እንደ ሰገደለት የሚገልጹ ምንባባት አሉ (ማቴ. 14÷33፤ 28÷9:17፤ ማር. 5÷6፤ ሉቃ. 24÷51-52፤ ዮሐ. 9÷38፤ ፊልጵ. 2÷10-11፤ ዕብ. 1÷6፤ ራእ. 1÷17፤ 5÷14)። ፍጥረት ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሰግድ አብ ፈቅዷል የሚል አስተያየት የሚሰጡ ሰዎች አሉ። ይህ ግን ስሕተት ነው። ምክንያቱም ብሉያትም ሆኑ ሐዲሳት ለአምላክ ብቻ እንድንሰግድ እርሱንም ብቻ እንድናመልክ በግልጽ ይናገራሉና (ዘፀ. 20÷3-5፤ ዘዳ. 5÷7-10፤ 6÷13-15፤ መዝ. 97÷7፤ ኢሳ. 45÷23)።

- አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ቃላት አማራጭ ትርጉም ስላላቸው፣ ክርስቶስን በሚያሳይ መልክ ስግደት በሚል ቃል የቀረቡትን ቃላት፣ አክብሮትን በሚያሳይ መልክ ብቻ ልንተረጉሞቸው ይገባል የሚሉም አሉ። ቃላት አማራጭ ትርጉም ሊወክሉ እንደሚችሉ እሙን ነው። ለአምላክ ስገዱ የሚሉ የብሉይ ኪዳን ምንባባት ለኢየሱስ ተጠቅሰው መገኘታቸው ግን፣ ቃሉ ለፍጥረት የሚሰጥን አክብሮት ለማመልከት ነው ልንል አንችልም። አምልኮን የሚያሳይ ስግደትን እንጂ።

- ሁለት ናሙናዎችን ብቻ እንመልከት ዕብራውያን 1÷6 “በኩሩን ወደ ዓለም ሲያገባ፣ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ” ይህ ክፍል ከዘዳግም 32÷43 እንዲሁም መዝሙር 96÷7 ላይ በቀጥታ የተጠቀሰ ነው። ምንም እንኳ ቃላት አማራጭ ትርጉም ቢኖራቸውም፣ በብሉይ ኪዳን ለያህዌ የተባለው፣ በቀጥታ ለኢየሱስ መነገሩ፣ አማራጭ ትርጉም ፍለጋ እንዳንዳክር ይገድበናል።

- በራእይ 5 ላይ ኢየሱስ ከአብ ጋር በአንድ ጉባኤ በእልፍ አእላፋት መላእክት፣ በአራቱ እንስሶችና በሃያ አራቱ ሽማግሌዎች እንደ ተሰገደለት እንመለከታለን። በዚህ ክፍል ስግደት የሚለው ቃል አምልኮን ሳይሆን ከበሬታን ብቻ የሚያሳይ ነው ልንል አንችልም። እንደዛ ከሆነ፣ ለአብም ስግደት አልቀረበም ማለት ነውና። በተጨማሪ በምዕራፉ ውስጥ በግንባራቸው ተደፍተው እንደ ጸለዩ፣ ዕጣንና አምልኮ ዝማሬ ማሕልት እንደ ነበር እንመለከታለን።

# አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት ናቸው

- **ማቴዎስ 28፥19**

1) “እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው”። “πορευθέντες οὖν μαθητεύσατε πάντα τὰ ἔθνη, βαπτίζοντες αὐτοὺς εἰς τὸ ὄνομα **τοῦ** πατρὸς καὶ **τοῦ** υἱοῦ καὶ **τοῦ** ἁγίου πνεύματος,”
2) ግራንቪል ሻርፕ የተባለው የሰዋሰው ሕግ (ሕግ #6)፣ ሁለት ተመሳሳይ ሙያ ያላቸው ስሞች “እና” (“ካይ” “καὶ”) በሚለው መስተጻምር ተያይዘው በስሞቹ መጀመሪያ ላይ ውስን መስተኣምር ካለ፣ ስሞቹ ስለ ተለያየ አካል የሚናገሩ ናቸው።
3) ይህ ዐይነት የሰዋስው አወቃቀር ያላቸውን የሚከተሉትን ክፍሎች በግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ይመልከቱ፤ ዮሐንስ 1÷17፤ ዮሐንስ 2÷22፤ ዮሐንስ 11÷44፤ 2ጢሞቴዎስ 1÷5።

# አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት ናቸው

## ሰላምታዎች

- “ከአባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን” “χάρις ὑμῖν καὶ εἰρήνη ἀπὸ θεοῦ πατρὸς ἡμῶν καὶ κυρίου Ἰησοῦ Χριστοῦ.”
- የግሪክን ሰዋስው ሕግ (የሻርፐስ ሕግ) ተከትለን ስንሄድ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን ፍንትው አድርጎ ያሳያል።
- የግራንቪል ሻርፕ ሕግ (ሕግ 5)፣ ሁለት ተመሳሳይ ሙያ ያላቸው ስሞች በ“እና” (“ካይ” “καὶ”) ተያይዘው በመጀመሪያው ስም ላይ ውስን መስተኣምር ከሌለ ስሞቹ ስለተለያየ አካል የሚናገሩ ናቸው። ሕጉ ስድስት ሕጎችን በጥምረት የያዘ ሲሆን፣ በዚህ ክፍል የምናየው ግን አምስተኛውን ሕግ ነው።
- ይህ የሰዋስው ሕግ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን የሚያስተምር ነው (ሮሜ 1÷7፤ 1ቆሮንቶስ 1÷3፤ 2ቆሮንቶስ 1÷2፤ ገላትያ 1÷3፤ ኤፌሶን 1÷2፤ ፊልጵስዩስ 1÷2፤ 2ተሰሎንቄ 1÷2፤ ፊልሞና 3፤ ኤፌሶን 6÷23፤ 1ተሰሎንቄ 1÷1፤ 2ተሰሎንቄ 1÷1፤ 1ጢሞቴዎስ 1÷1-2፤ 2ጢሞቴዎስ 1÷2፤ ቲቶ 1÷4፤ ያዕቆብ 1÷1፤ 2ዮሐንስ 3)።

# ሀ. አብ ወልድ አይደለም

1) አብና ወልድ ይዋደዳሉ (ዮሐ. 3÷35፤ 5÷20፤ 14÷31፤ 15÷9፤ 17÷23-26፤ ማቴ. 3÷17፤ 17÷5፤ 2ጴጥ. 1÷17)።

2) አብና ወልድ ይተዋወቃሉ (ዮሐ. 7÷28-29፤ 7÷29፤ 8÷55፤ 10÷15፤ማቴ. 11÷27፤ ሉቃ. 10÷22)።

3) አብና ወልድ ይከባበራሉ (ዮሐ. 17÷1:4-5፤ 8÷54፤ 15÷8፤ 8÷49፤ 17÷4፤ 12÷28፤ 13÷31፤ ዕብ. 5÷5፤ ማቴ. 6÷9፤ ሉቃ. 11÷2)።

4) አብና ወልድ ይነጋገራሉ (ዮሐ. 11÷41-42፤ 12÷27-30፤ 17÷1-26፤ 6÷11፤ ማቴ. 26÷26:36-44፤ 8÷6፤ ሉቃ. 24÷30) ሲነጋገሩም ሰዎች ሰምተዋል (ዮሐ. 12÷28-29)።

5) አብ ለወልድ ይላካል (ዮሐ. 17÷18፤ 20÷21፤ 3÷16-17፤ ገላ. 4÷4፤ 1ዮሐ. 4÷10)።

6) በፍርድ አደባባይ አብ ለወልድ ይመሰክራል (ዮሐ. 5÷31-32፤ 8÷16-18:28፤ 12÷49)።

7) አብና ወልድ ዕብረው በጋራ ኖረዋል፤ ይኖራሉም (ዮሐ. 1÷1፤ 17÷5፤ 8÷58፤ 1ዮሐ. 2÷1)።

8) ወልድ ነፍሱን ለአብ ዐደራ ሰጥቶአል (ማቴ. 15÷34፤ 23÷46፤ ሐሥ. 7÷59)።

9) አብና ወልድ የተለያየ ፈቃድ አላቸው (ሉቃ. 22÷42፤ ማቴ. 26÷39:42፤ ማር. 14÷36፤ ዮሐ. 18÷11፤ 5÷30)።

10) አብና ወልድ፣ "አንተ"፣ "እኔ" ይባባላሉ (ዮሐ. 14÷16፤ 14÷26፤ 15÷26፤ 16÷15)።

11) ኢየሱስ ጠበቃችን በአብ "ዘንድ" ነው ያለው 1ዮሐንስ 2÷1፤ ዮሐንስ 1÷1፤ ዮሐንስ 17÷5። በግሪኩ ሰዋስው "ጋር"፣ "ዘንድ" (ግሪክ "ፕሮስ" "πρὸς") የሚለው በተሳቢ ሙያ (Objective case) በሚቀደምበት ጊዜ መስተጋብርን (ግንኙነትን) ያመለክታል።

12) ኢየሱስ ሲሞት ነፍሱን ለአባቱ ዐደራ መስጠቱ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን ያሳያል (ማርቆስ 15÷34፤ ሉቃስ 23÷46 እስጢፋኖስ በሚሞትበት ጊዜ ነፍሱን ለኢየሱስ ክርስቶስ ዐደራ እንደ ሰጠው ማለት ነው ሐዋርያት ሥራ 7÷59)።

13)ኢየሱስ አባቱን፣ “የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ ፈቃድ ይሁን” ሲል መጸለዩ (ሉቃስ 22÷42)፣ አብ የራሱ ፈቃድ እንዳለው ሁሉ ወልድም የራሱ ፈቃድ እንዳለው የሚያሳይ ነው።

14)ኢየሱስ እምቅድመ ዓለም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር! የሐንስ **1÷1-18፤** ዮሐንስ **8÷56-59፤** ዮሐንስ **16÷28**

15)ኢየሱስ፣ ከሰማይ የመጣ፣ ከአብ የተላከ፣ ወደ ሰማይ የወጣ፣ ወደ አባቱ የተመለሰ ነው፤ ዮሐ. 3÷13:31፤ 6÷33:38: 41:46:51: 56-58:62፤ 8÷23:42፤ 13÷3፤ 16÷27-28፤ ከሐዋርያት ሥራ 1÷10-11 ጋር ያወዳድሯል፤ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ከመላኩ ጋር ያወዳድሯል ዮሐንስ 16÷5-7፤ 1ጴጥሮስ 1÷12።

# ለ. ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይደለም

1) ኢየሱስ ራሱ መንፈስ ቅዱስ፣ "ሌላ አጽናኝ" እንደ ሆነ ገልጾአል (ዮሐንስ 14÷16፤ ከ1ዮሐንስ 2÷1 ጋር ያወዳድሯል)።
2) ኢየሱስ፣ መንፈስ ቅዱስን ልኮታል (ዮሐንስ 15÷26፤ 16÷7)። ይህ ደግሞ ኢየሱስ ላኪ፣ መንፈስ ቅዱስ ተላኪ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ላኪና ተላኪ አኃዛዊ አንድነት አላቸው ማለት ስሕተት ነው።
3) መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን እንደሚያከብር መናገሩ ለወልድ ራሱን ዝቅ ማድረጉን ያሳያል (ዮሐንስ 16÷13-14)። ይህ ደግሞ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን ታሳቢ ያደረገ ንግግር ነው።
4) ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት መሆናቸው (ወልድ የራሱ አካል እንዳለው ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስም የራሱ አካል እንዳለው) በማቴዎስ 28÷19 ላይ ተገልጾአል። በማቴዎስ 28÷19 ላይ ያቀረብነውን ሰፊ ሰዋስዋዊ ሙግት ይመለከቷል።
5) መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ በእርግብ አምሳል ወርዶበታል (ሉቃስ 3÷22)።

# ሐ. መንፈስ ቅዱስ አብ አይደለም

1) አብ መንፈስ ቅዱስን ልኮታል፤ አብ ላኪ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ተላኪ እስከ ሆነ ድረስ፣ አንድ አካል ናቸው ማለት አይቻልም (ዮሐንስ 14÷15፤ 15÷26)። በዚህ ዐውድ ውስጥ አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው ማለት የሚቻለው፣ "ላከ" የሚለው ቃል በቀጥታ (ቊማዊ) ትርጒም ሳይሆን፣ ተምሳሌታዊ ገለጻ አለው የሚል ማስረጃ ሲኖረን ብቻ ነው።

2) መንፈስ ቅዱስ ወደ አብ ለአማኞች ይማልዳል (ሮሜ 8÷26-27)። ምልጃን ማቅረብ ማላጁ፣ ተማላጁን ወክሎ መቅረብ ሲችል ብቻ ነው። ይህ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና እንዳለው እንዲሁም ከአብ የተለየ የማንነት ባለቤት እንዳለው የሚመሰክር ነው።

3) አብና መንፈስ ቅዱስ ሁለት የተለያዩ አካላት መሆናቸው በማቴዎስ 28÷19 ላይ በግልጽ ተመልክተናል።

# ለአርዮሳውያኑና ለሰባልዮሳውያኑ ሙግት ከትካች ዐጸፋ

## ሀ. የአርዮሳውያኑ ሙግት

### 1) ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ነው

### የአርዮሳውያኑ ዐዋጅ

ምሳሌ 8÷22፣ "እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ፤ በቀድሞ ሥራው መጀመሪያ" ክፍሉ ስለ ጥበብ ነው የሚያወራው። ስለ እግዚአብሔር ጥበብ አይደለም ምክንያቱም እግዚአብሔር የራሱን ጥበብ ሊፈጥር አይደለም። ስለዚህ ክፍሉ ስለ ሌላ ጥበብ ነው የሚናገረው። በአንደኛ ቆሮንቶስ 1÷24 ክርስቶስ፣ "ጥበብ" ተብሎአል፤ ስለዚህ ምሳሌ 8 የሚናገረው ስለ ክርስቶስ ነው። ይህም የሚያሳየው ክርስቶስ እንደ ተፈጠረ ነው።

# ከትካች ዐጸፋ

- በምሳሌ መጽሐፍ ከምዕራፍ 1-9 ባሉት ክፍሎች ሁሉ፣ ጥበብ በሰውኛ አነጋገር (personification) ጥቅም ላይ ውሎአል። ስለዚህ ምሳሌ 8÷22-31 ስለ ክርስቶስ ይናገራል ማለት ትክክል አይደለም። የምሳሌ መጽሐፍ ፍጹም ቅኔያዊ በመሆኑ፣ ከአንደኛ ቆሮንቶስ 1÷24:30 ጋር በማያያዝ ክፍሉ ስለ ክርስቶስ ይናገራል ማለት አግባብ አይደለም።
- ዳዊት መሰንቆንና በገናን ተነሡ እንደሚለው ማለት ነው፣ "በገና ሆይ ተነሥ መሰንቆም እኔም ማልጄ እነሣለሁ" (መዝ. 108÷2)። ክፍሉ ስለ ጥበብ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ ነው የሚናገረው ካልን የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ የግድ ይኖርብናል:—

1) ክፍሉ ጥበብን በአነስታይ (feminine) ነው የሚጠራት (ቍጥር 1:2:3:11)፤ ክርስቶስ በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው "አንቺ" (she) የተባለው?

2) ምሳሌ 8 የሚናገረው ስለ ጥበብ ብቻ ሳይሆን ስለ ማስተዋልም ጭምር ነው (ቍጥር 1)። አንደኛ ቆሮንቶስ 1÷24:30 በመጥቀስ ክርስቶስ ጥበብ ነው ካልን፣ ማስተዋልስ ደግሞ ማን ሊሆን ነው?

4) “ጥበብ ቤትዋን ሠራች ሰባቱንም ምሶሶዎችዋን አቈመች” (9÷1) ሲልስ ምን ማለቱ ነው?

5) ሰሎሞን ስለ ክርስቶስ የሚናገር ከሆነ፣ “በውኑ ጥበብ አትጮኽምን? ማስተዋልስ ድምፅዋን አትሰጥምን?” በማለት፣ ሰውኛ አገላለጽ መጠቀም ለምን አስፈለገው?

6) ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ከሆነ፣ በአንጻሩ የእግዚአብሔር ኀይል ጥበብ ክርስቶስ ከሆነ (1ቆሮ. 1÷24)፣ እግዚአብሔር ክርስቶስን ከመፍጠሩ በፊት ኀይልና ጥበብ የለውም ነበር ማለት ነው?

7) በምሳሌ መጽሐፍ ውስጥ ጥበብ እንደሚገዛ ንብረት ነው የቀረበችው (1÷5፤ 4÷5፤ 15÷32፤ 16÷16፤ 17÷16፤ 18÷15፤ 19÷8፤ 20÷14፤ 23÷23) እነዚህስ ክፍሎች ስለ ኢየሱስ የሚያወሩ ናቸው ማለት ነው?

# የአርዮሳውያኑ ዐዋጅ

በቈላስይስ 1÷15፣ "ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው" ይላል። በኵር የሚለው ቃል የሚያሳየን፣ በመወለድ ሂደት ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ መሆኑን ነው። ይህም የሚያረጋግጥልን ኢየሱስ ክርስቶስ በይሖዋ አምላክ እንደ ተፈጠረ ነው። ራእይ 3÷14 ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው" ይለዋል፤ ከዚህ ዐረፍተ ነገር በቀላሉ የምንማረው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሖዋ አምላክ ከፈጠራቸው ፍጥረታት፣ የመጀመሪያ ፍጡር መሆኑን ነው።

# ከትካች ዐጸፋ

- ቈላስይስ 1÷15 "በኵር" (ግሪክ:— "ፕሮቶቶኮስ" "πρωτότοκος") የሚለው ቃል፣ በመወለድ ቅደም ተከተል የመጀመሪያ ማለት ሳይሆን፣ ክርስቶስ የፍጥረታት ሁሉ ወራሽና ባለቤት መሆኑን የሚያስተምር ነው።
  - "በኵር" ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል፣ በብሉይ ኪዳን የበኵር ልጆች ከሌላው ልጅ ይልቅ ያላቸውን መብት የሚያሳይ ነው።
  - ንጉሥ ዳዊት (መዝሙር 89÷27)።
  - የዮሴፍ የመጀመሪያ ልጅ ምናሴ ሆኖ ሳለ (ዘፍ. 41÷50-51)፣ ኤፍሬም፣ "በኵር" ተብሎአል (ኤር. 31÷9)።
  - ያዕቆብ የኤሳውን ብኵርና ወሰደ ስንል፣ "ክብሩን" ወሰደ ማለታችንም አይደል?
  - ኤፍ ኤፍ ብሩስ የተባለው ታዋቂው እንግሊዛዊ ሊቅ፣ ጳውሎስ በቈላስይስ 1÷15 ላይ የኢየሱስን ፍጡር መሆን ለማመልከት ቢፈልግ ኖሮ፣ "ፕሮቶቶክስ" ከሚለው የግሪክ ቃል ይልቅ፣ "ፕሮቶኪቲሲስ" የሚለውን ቃል ይጠቀም ነበር የሚለውን አስተያየት የሰጠው በዚህ አግባብ ነው።
  - "የይሖዋ ምስክሮች" በቈላስይስ 1÷15 ላይ አራት ጊዜ "ሌሎች ነገሮች" (other) የሚለውን ቃል በዐዲሱ ዓለም ትርጒም ላይ ጨምረዋል።

# የአርዮሳውያኑ ዐዋጅ

- ራእይ 3÷14 የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት "አርኬ" (ἀρχή) የሚለውን የግሪክ ቃል፣ "ከአምላክ ፍጥረት የመጀመሪያ የሆነው" ሲል ተርጉሞታል።
- ቃሉ በዐዲስ ኪዳን የጊዜን ጅማሬ ለማሳየት (ዮሐ. 1÷1:2፤ 6÷64፤ 8÷25:44፤ 15÷27፤ 16÷4፤ 1ዮሐ. 1÷1፤ 2÷7:13:14:24፤ 3÷8:11፤ 2ዮሐ. 5-6) እንዲሁም በብዙ የዐዲስ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ፣ "መገኛ" ወይም "ምንጭ" በሚለው ትርጒሙ ጥቅም ላይ ውሏል (ሉቃ. 12÷11፤ ሮሜ. 8÷38፤ 1ቆሮ. 15÷4፤ ኤፌ. 1÷21፤ 3÷10፤ 6÷12፤ ቈላ. 1÷16፤ 2÷10፣ 15፤ ቲቶ 3÷1)።
- በራእይ መጽሐፍ ቃሉ እግዚአብሔርን ለማመልከት ገብቶአል ወይም ጥቅም ላይ ውሎአል (ራእ. 21÷6፤ 22÷13)።

# ከትካች ዐጸፋ

- ቃሉ በዐዲስ ኪዳን የጊዜን ጅማሬ ለማሳየት (ዮሐ. 1፥1:2፤ 6፥64፤ 8፥25:44፤ 15፥27፤ 16፥4፤ 1ዮሐ. 1፥1፤ 2፥7:13:14:24፤ 3፥8:11፤ 2ዮሐ. 5-6) እንዲሁም በብዙ የዐዲስ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ፣ "መገኛ" ወይም "ምንጭ" በሚለው ትርጒሙ ጥቅም ላይ ውሏል (ሉቃ. 12፥11፤ ሮሜ. 8፥38፤ 1ቆሮ. 15፥4፤ ኤፌ. 1፥21፤ 3፥10፤ 6፥12፤ ቈላ. 1፥16፤ 2፥10፣ 15፤ ቲቶ 3፥1)።
- በራእይ መጽሐፍ ቃሉ እግዚአብሔርን ለማመልከት ገብቶአል ወይም ጥቅም ላይ ውሎአል (ራእ. 21፥6፤ 22፥13)።

- ከዐዲሱ ዓለም ትርጒም በስተቀር፣ በየትኛውም የእንግሊዝኛም ሆነ የዐማርኛ ትርጒሞች ላይ፣ ቃሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ነው አይልም።
  - የ1980 ትርጒም፣ "ለእግዚአብሔር ፍጥረት መገኛ" ብሎ ሲተረጒመው፣
  - ዐዲሱ መደበኛ ትርጒም ደግሞ፣ "የእግዚአብሔርም ፍጥረት ምንጭ" የሆነው ሲል፣ ተርጒሞታል።
  - የ1954 ትርጒም፣ "አርኬ" (ἀρχή) የሚለውን የግሪክ ቃል "መጀመሪያ" ብሎ ይተርጒመው እንጂ፣
  - "አምላክ ፍጥረትን ሲፈጥር ከእርሱ ጋር መጀመሪያ የነበረ" ለማለት ነው ወይስ፣ "እርሱ ራሱ የመጀመሪያው የአምላክ ፍጥረት ነው" የሚለው ጒዳይ ግልጽ አይደለም (እባክዎን የ1954 ትርጒምን በጥሞና ይመልከቱ)።

እንደ ዐማርኛው ሁሉ፣ የእንግሊዝኛም ትርጒሞች “አርኬ” (ἀρχή) የሚለውን የግሪክ ቃል በተለያየ መልኩ ተርጒመውታል።

- ለምሳሌ:— “ኒው ኪንግ ጀምስ ትርጒም” (NKJV) እና “ኒው አሜሪካን ስታንዳርድ ባይብል” (NASB) “መጀመሪያ” ብለው ሲተረጒሙት፣
- እንደ “ኒው ሪቫይዝድ ስታነዳርድ ቨርዥን” (NRSV) ያሉ ትርጒሞች፣ “መገኛ” (“origin”) ብለው ተርጒመውታል።
- “ኒው አሜሪካን ባይብል” (NAB) “ምንጭ” ሲለው፣
- “ኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን” (NIV) ደግሞ “መሪ” (“ruler”) ብሎታል።

- ክፍሉ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጡርነት የሚያሳይባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው:—
  - **አንደኛ፡** በዚሁ በራእይ ዮሐንስ መጽሐፍ ውስጥ፣ “አርኬ” (ἀρχή) የሚለው የግሪክ ቃል የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል፣ “አልፋና ዖሜጋ፤ መጀመሪያውና መጨረሻው” (22፥6፤ 22፥13)።

  - **ሁለተኛ፡** የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ራሱ፣ “አርኬ” (ἀρχή) የሚለውን የግሪክ ቃል በተለያየ መልክ ተርጉሞታል፣ ለምሳሌ:— “መስተዳድር” (1ቆሮ. 15፥24፤ ኤፌ1፥21፤ 3፥10)፣ “ሹማምንት” (ሉቃስ 12፥11)፤ “መንግሥታት” (ሮሜ 8፥38)፤ “ሥልጣናት” (ቲቶ 3፥1)። በራእይ ዮሐንስ ላይ ደግሞ፣ “ገዢ” ብለው ተርጉመውታል (ራእይ 1፥5)። ይህ እውነት ከሆነ፣ የቃሉን አማራጭ ትርጒም የሚወስነው ቃሉ የሚገኝበት ዐረፍተ ነው (ይህ ደግሞ ለሥነ ትርጓሜ ወሳኝ ሕግ መሆኑን ያስተውሏል)።

  - **ሦስተኛ፡** በራእይ ዮሐንስ ላይ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ክርስቶስ፣ “አልፋና ዖሜጋ ተብሏል” 1፥8፤ “ፊተኛውና መጨረሻው” ተብሏል፣ 1፥17-18፤ 22፥12-13 ይህ ደግሞ ራእዩ ምዕራፍ አንድ፣ ኢየሱስ ጅማሬ የሌለው ፍጻሜ የሌለው ነው እያለ፣ መልሶ ፍጡር/ተፈጣሪ ነው ሊለን አይችልም። “አልፋና ዖሜጋ ፊተኛውና መጨረሻው” የሚለው ገለጻ ዘላለማዊነትን ያመለክታል እየተባለ፤ ተመልሶ ተፈጥሯል የሚለው ጉዳይ ተቃርኖ ነው።

## 2) ኢየሱስ ከአብ ያንሳል

- ኢየሱስ ከአብ እንደሚያንስ የሚናገሩ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስላሉ፣ ኢየሱስን ከአብ እኩል ፍጹም አምላክ ማድረግ እንችልም ባዮች ናቸው ዮሐ. 5÷19፤ 5÷30፤ 6÷38፤ 14÷28፤ 20÷17፤ ማቴ. 26÷39፤ ሉቃ. 22÷42፤ 1ቆሮ. 11÷3፤ 15÷27-28፤ ዕብ. 5÷7-8፤ 10÷7:9።

# ከትካቹ ዐጸፋ

- ማነስ ስንል ከምን አንጻር የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ ይኖርብናል። በሥራ ክፍፍል ደረጃ ማነስ (Functional Subordination) ነው ወይስ በማንነት (Functional Subordination) ወይም በተፈጥሮ ማነስ ነው የሚለው ጉዳይ እጅግ ዋነኛ ነው።

- መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል ሆኖ ሳለ በራሱ ፈቃድ ትስጉት በመሆኑ፣ ራሱን ለአብ ዝቅ እንዳደረገ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል ፊልጵ. 2:5-8።

  - ሚስቶች ሆይ ለባሎቻችሁ ተገዙ (**ὑποτάσσομαι**) ኤፌ 5÷22-24፤ ቈላ. 3÷18፤ ቲቶ 2÷4-5፤ 1ጴጥ. 3÷1:5-6
  - ባሮች ሆይ ለጌቶቻችሁ ተገዙ (**ὑποτάσσομαι**) (ኤፌ. 6÷5-7፤ ቈላ. 3÷22-23፤ 1ጢሞ. 6÷1-2፤ ቲቶ 2÷9-10፤ 1ጴጥ. 2÷18)።
  - ለበላይ ባለሥልጣናት ተገዙ (ሮሜ 13÷1-2፤ ቲቶ 3÷1፤ 1ጴጥ. 2÷13-14)።
  - የነቢያት መንፈስ ለነቢያት ይገዛል (**ὑποτάσσομαι**) (1ቆሮ. 14÷29-32)

# ማጠቃለያ

- ኢየሱስ ፈጣሪ መሆኑን እንጂ መፈጠሩን የሚናገር አንዳችም የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የለም።

- ኢየሱስ ለአባቱ መገዛቱ ትስጉት የመሆን፣ ትሕትናውን እንጂ በባሕርዮቱ ከአብ ማነሱን የሚያመለክት አይደለም።

# ለ. የሰባልዮሳውያኑ ሙግት

- ሰባልዮሳውያኑ ኢየሱስና አብ አንድ አካል ናቸው ለማለት የተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ይጠቅሳሉ። ለእነዚህ ጥቅሶች ከትካች ዐጸፋ አቀርባለሁ።

ኢሳ. 9፥6፤ ዮሐ. 10፥30፤ ዮሐ. 14፥9

# “ሕፃን ተወልዶልናልና፤ ወንድ ልጅ ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም፣ ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ የዘላለም አባት፣ የሰላም ልዑል ይባላል”

ኢሳይያስ 9፥6

አንደኛ፤ “በብሉይ ኪዳንም ሆነ በዕብራውያንና በዐረቡ ባህል፣ “አባት” (በዕብራይስጡ፣ “አብ” “אָב”) በተጸውዖ (በመጠሪያ) ስምነት ካገለገለ፣ የስሙ ባለቤት (በዚህ ቃል የሚጠራው ግለሰብ) ከሚጠራበት ስም ጋር አንድ ዐይነት ባሕርይ አለው ማለት ነው”።

- “**አቢዓልቦን**” (אֲבִי־עַלְבוֹן ) (2ሳሙኤል 23÷31) የሚለው ጣምራ ስም “አቢ” “אָב” ማለትም “አባት” እንዲሁም “ዓልቦን” “עַלְבוֹן ” ማለት “ጠንካራ” ከሚሉት ቃላት የተዋቀረ ነው። በተገናኝ ሲነበብ (አጫፍረን ስናነበው)፣ የጥንካሬ አባት ወይም እጅግ በጣም ጠንካራ የሚል ትርጒም ይወክላል። “**አቢያሳፍ**” “אֲבִיאָסָף” (ዘፀአት 6÷24) ማለት፣ “አቢ” “אָב” “አባት” እንዲሁም “አሳፍ” “אָסָף” ማለት “ሰብሳቢ” አዛርፈን ስናነበው፣ “በሰብሳቢነት ትልቅ ስም የተጐናጸፈ” ማለት ነው። “**አቢጋኤል**” “אֲבִיגַיִל” (1ዜና. 2÷16) ማለት፣ “አቢ” “אָב” “አባት” እንዲሁም “ጋኤል” ማለት “ጠንካራ” በተገናኝ፣ “የጥንካሬ አባት” ወይም “እጅግ በጣም ጠንከር ያለች” ማለት ነው - አቢጋኤል የሚለው ስም የሴት መጠሪያ መሆኑን ልብ ይሏል። አባት ነሽ ማለት ሳይሆን፣ ከፍ ያልሽ ነሽ ማለት ብቻ ነው (በዐማርኛ “ላቀች” ከሚለው ስም ጋር የሚጐዳኝ ይመስላል)።

- በዐጭሩ፣ “አብ” ወይም አባት (በዕብራይስጡ፣ “בָּא”) የሚለው ቃል አባትነትን የሚያሳይ ሳይሆን፣ ከፊት ለፊቱ ያለውን ስም የሚያደምቅ ቅጽል ነው፤ ይኸውም “የጥንካሬ አባት”—በጣም ጠንካራ፤ “የመሰብሰብ አባት”—እጅግ በጣም ታላቅ ሰብሳቢ፤ “ከፍ የማለት አባት”—እጅግ በጣም ከፍ ያለች...ወዘተ ማለት ነው።

  በዚህ ክፍል “አባት” (“בָּא”) የሚለው ቃል አባትነትን አመላካች ነው ከተባለ፣ “ጥንካሬ የሚባልን ሰው

- የወለደ ወላጅ”፣ “መሰብሰብን የወለደ አባት” ወዘተረፈ የሚል ትርጓሜ ሊይዝ ነው ማለት ነው። ይህ መቼም የቋንቋ ባለቤት ለሆነ የሰው ዘር እንግዳ አካሄድ ነው። አንዳችም ትርጒም ሊወክልም አይችልም፤ ምክንያቱም መሰብሰብ፣ ጥንካሬ፣ ከፍ ማለት ወዘተ የሚሉት ስያሜዎች የሚወለዱ ልጆች፣ ወላጅ አባት የሚፈልጉ ሕያዋን አይደሉምና። ይህ ዐይነቱ ፍቺ ስሑት መሆኑ የሚያግባባን ከሆነ፣ “አብ” የሚለው ቃል ማድመቂያ ቅጽል እንጂ፣ አባትነትን የሚያሳይ ስም አይደለም።

- በኢሳይያስ 9÷6 ላይ፣ “የዘላለም አባት” ተብሎ የተተረጐመው ቃል በዕብራይስጥ “አቢአድ” “אֲבִיעַד” ከሁለት ስሞች የተጫፈረ (የተዛረፈ) ስያሜ ነው። ይኸውም፣ “አብ” እና “አድ” ከሚሉት ቃላት ሲሆን፣ ትርጒሙም “አባት” እና “ዘላለም” ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከላይ እንዳየናቸው፣ “በአባት” እንደ ተጫፈሩ ስያሜዎች፣ የክርስቶስን ዘላለማዊነት የሚያሳይ እንጂ (“የዘላለም አባት መሆኑን” ዕብራውያን 1÷2፤ 11÷3፤ ራእይ 1÷7-8፤ 1÷17-18፤ 2÷8፤ 22÷13)፣ “ኢየሱስ አብ ነው” ወይም “አብና ወልድ አኃዛዊ አንድነት አላቸው” ወይም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ፣ “የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት” (2ቆሮንቶስ 1÷3) ነው የሚል አንዳችም ዐሳብ የለውም።

ሁለተኛ፤ “አባት” (በዕብራይስጡ፣ “አብ” “בָּא”) የሚለው ቃል ዘላለማዊነቱን የሚያዳምቅ/የሚቀጽል ሳይሆን፣ ኢየሱስ አባት መሆኑን የሚያመለክት ነው ቢባል እንኳ (እንደዚያ እንዳልሆነ በተራ ቊጥር አንድ ላይ በግልጽ ለማሳየት ሞክረናል)፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ ነው ማለት አይደለም። እኔ አባት ነኝ፤ ነገር ግን እኔ የራሴ አባት አይደለሁም። ኢየሱስ “አባት” ቢሆን እንኳ፣ ከፍጡራን ጋር ያለውን ግንኙነት አመላካች እንጂ፣ ኢየሱስ ራሱ፣ “አባቴ” የሚለው አብ ነው ማለት አይደለም (አባት፣ ልጅ፣ እናት፣ ወንድም፣ እኅት ወዘተ የሚሉት ቃላት ግንኙነትን አመላካች እንዲሁም ተነጻጻሪ ቃላት መሆናቸው በጭራሽ ሊጠፋን አይገባም። አባት የሚለው ቃል ልጆችን ታሳቢ ያደረገ ወይም የፍጥረት ባለቤትነቱን አስተማሪ ነው)።

# “እኔና አብ አንድ ነን”
# “ἐγὼ καὶ ὁ πατὴρ ἕν ἐσμεν”
# ዮሐንስ 10፥30

**አንደኛ፤** ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ አብ ነኝ ለማለት ፈልጎ ቢሆን ኖሮ፣ “እኔ አብ ነኝ” ወይም፣ “አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው” ማለት ነበረበት። ምክንያቱም ይህ መደበኛው አነጋገር እንዲሁም በሰዋስው ትክክለኛ አገባብ ነውና። በዚህ ቦታ ላይ የተገለጸው ግን፣ “እኔና አብ አንድ ነን” የሚል እንጂ፣ “እኔ አብ ነኝ” የሚለው አይደለም።

**ሁለተኛ፤** “እኔና አብ አንድ ነን” በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ፣ “አንድ ነን” ተብሎ ወደ ዐማርኛ የተተረጐመው ሐረግ፣ “ሔን ኤስሜን” (“ἕν ἐσμεν”) የሚለው የግሪክ ቃል ነው፤ ይህ ደግሞ፣ ብዙ ቍጥር የሚያመለክት አንደኛ መደብ ነው፤ ይህ ኢየሱስ አብ ቢሆን ኖሮ፣ “ኢስሜን” (“ἐσμεν”—“we are”) የሚለውን ቃል ሳይሆን፣ አንደኛ መደብ ነጠላ ቍጥር የሆነውን “ኢጎ” ወይም “ኢጎ ሂሚ” (“ἐγὼ/ εἰμί”-“I am”) የሚለውን የግሪክ ቃል ይጠቀም ነበር።

**ሦስተኛ፤** ኢየሱስ በዚሁ ክፍል አብን፣ “አባቴ” (ቊጥር 32) እንዲሁም፣ “የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ” (ቊጥር 36) የሚሉትን ቃላት እየተናገረ፣ መልሶ ራሱን፣ “አባት” ያደርጋል ማለት ስሕተት ነው።

**አራተኛ፤** በክፍሉ ውስጥ ኢየሱስ “አንድ” (ግሪኩ “ሂን” “ἕν”) የሚለውን ቃል የተጠቀመው የአካል አንድነትን ለማሳየት ነው ከተባለ፣ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ኢየሱስ፣ “እኛም [አብና ወልድ] አንድ እንደ ሆንን፣ አንድ ይሆኑ ዘንድ” (ዮሐንስ 10÷30 ከ17÷21-23 ጋር ያነጻጽሩ) ሲል፣ ለደቀ መዛሙርቱ የጸለየው ጸሎት፣ ደቀ መዛሙርቱ የዐላማ ወይም የልብ አንድነት እንዲኖራቸው ሳይሆን፣ የአካል አንድነት እንዲኖራቸው ነው ማለት ነው፤ ይህ ደግሞ እንግዳ ዐስተሳሰብ ነው።

## “ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ ‘አንተ ፊልጶስ! ይህን ያህል ጊዜ ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ፣ ‘አብን አሳየን’ ትላለህ?’”

ዮሐንስ 14፥9

አንደኛ፤ “እኔን ያየ አብን አየ” (Ὁ ἑωρακὼς ἐμὲ ἑώρακεν τὸν Πατέρα) በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ቊልፍ ቃል “ማየት” (“ሂሆራኮስ” ἑωρακὼς) የሚለው ግሥ ነው። በዚህ ዐውድ ማየት የሚለው ግሥ ቊማዊ አይደለም ስለዚም በዐይነ ሥጋ ኢየሱስን ማየት አብን ማየት ነው ብለን ልንተረጉምምው አንችልም።

ሁለተኛ፤ በቊጥር 6 ላይ ኢየሱስ፣ “መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ” የሚለውን ጉዳይ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በቊጥር 7 ሲያብራራ፣ እርሱን ማወቅ ማለት አብን “ማወቅ” እንዲሁም አብን “ማየት” ማለት ነው፤ መንገዱ እርሱ ነውና።

ሦስተኛ፤ በምዕራፍ 14 ኢየሱስ ራሱን ከአብ ለመለየት፣ “እኔ” ወይም “የእኔ” (ግሪክ εἰμι, με, ἐμὲ, ἐγὼ) የሚሉትን የመጀመሪያ መደብ ተውላጠ ስሞችን ሲጠቀም፣ ወልድን ለማሳየት ደግሞ፣ ሦስተኛ መደብ ተውላጠ ስሞችን (እርሱ፣ የእርሱ αὐτον, αὐτοῦ) ተጠቅሞአል። ይህ ሁኔታ አብና ወልድ የተለያዩ መሆናቸውን በግልጽ የሚያሳይ ነው። ልክ እንደዚሁ ሁሉ ኢየሱስ ራሱን ከመንፈስ ቅዱስ የተለየ አድርጎ ያቀረበውም እነዚህን ተውላጠ ስሞች በመጠቀም ነው፣ “እኔ [κἀγὼ—and I] አብን እለምናለሁ፤ እርሱም [δώσει—he will give] ከእናንተ ጋር ለዘለዓለም የሚኖር ሌላ [ἄλλον] አጽናኝ ይሰጣችኋል” (ዮሐንስ 14÷16፤ እንዲሁም ቁጥር 7:10:26 ይመለከቷል)።

# ቁጥር 1. “በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም ደግሞ እመኑ” (“πιστεύετε εἰς τὸν θεὸν καὶ εἰς ἐμὲ πιστεύετε.”)

ቁጥር 2. “በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ” (“τοῦ πατρός μου μοναὶ πολλαί εἰσιν”)።

ኢየሱስ አባቱን “የእኔ አባት” (“τοῦ πατρός μου”) ሲል የጠራበት ተሳቢ ሙያ (genitive case)፣ አባት ልጅ እንዳልሆነ ልጅም አባት እንዳልሆነ፣ ነገር ግን አባትና ልጅ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

ቁጥር 7-11 ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ከአብ እንደሚለይ የሚገልጹ መስተዋድዶችን በንግግሩ ውስጥ ተጠቅሞአል:— “በእኔ (πρὸς) በቀር ወደ (δι’) አብ የሚመጣ የለም” (ቊ.6)፣ “እኔ በአብ (ἐν) እንዳለሁ አብም በእኔ (ἐν) እንዳለ” (ቊ.10)፣ “በእኔ (ἐν) የሚኖረው አብ” (ቊ. 10)። እነዚህ መስተዋድዶች አብና ወልድ የተለያዩ አካላት እንደ ሆኑ ግልጽ አድርጎ ባስቀመጠበት ዐውድ ውስጥ፣ የተወሰኑ ሐረጎችን ከዐውደ ምንባቡ ዐሳብ ፈልቅቄ በማውጣት፣ ኢየሱስና አብ አንድ አካል ናቸው ብሎ ማስተማር ለአምላክ ቃል ተገቢውን ክብር ያለመስጠት ነው።

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር ዘአፈጸመነ

# በዳኅና